የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

# Escalating Government Crackdown in Ethiopia

January 24, 2015

For Immediate Release

The Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo) has learnt that the ruling TPLF/EPRDF is now intensifying its crackdown on the opposition in Ethiopia. Ahead of the planned demonstration organized by Unity for Democracy and Justice Party (UDJ) for tomorrow, January 25, 2015, security forces have now arrested at least four members of the leadership of UDJ including :

- Asrat Abraham , Head of Public Relations
- Selomon Seyoum, Editorial Board member of UDJ's publication " the Millions Voice "
- Sintayehu Chekol, Head of the youth Department , UDJ Addis Ababa branch
- Neway Gebeyehu , a Deputy in Public Relations Department of UDJ

The protest demonstrations which are expected to take place in Addis Abeba, Bahirdar, Arbaminch...etc, are organized to protest against the government's and its election board's actions to block UDJ and All Ethiopia Unity Party (AEUP) from participating in the May 2015 federal election.

Shengo would like to alert the international community on the escalating government crackdown and possible violence against Ethiopians exercising their legal rights to peaceful protest and freedom of association. In this regard, Shengo would like to ask the international community, particularly the donor countries, to use their leverage and interfere to stop the escalating repression before it is too late.

We also want to put the ruling party on notice to refrain from such violent and anti-democratic practices and to stop all forms of harassment and intimidation immediately.

We express our unequivocal solidarity with political parties as well as the people of Ethiopia who are exercising their basic rights in a peaceful way.

## በኢትዮጵያ ውስጥ አገዛዙ የሚያካሂደው አፈና ተጠናክሮ ቀጥሏል

ጥር 16፣ 2007
ለአስቸኳይ ስርጭት

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) እራሱን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጫነው አገዛዝ በተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ አፈናውን አጠናክሮ የቀጠለ መሆኑን ለመረዳት ችሏል። በነገው ዕለት (ጥር 17 ቀን 2007 ዓ. ም) በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትኅ ፓርቲ (አንድነት)

አስተባባሪነት ሊደረግ ከታሰበው ሰላማዊ ሰልፍ አስቀድሞ የአገዛዙ የፀጥታ ኃይሎች ቢያንስ አራት የአንድነት ፓርቲ የአመራር አባላትን ማሰራቸውን ሸንጎ ተገንዝቧል። ከታሰሩት ውስጥ፦

1. አቶ አሥራት አብርሃም - የአንድነት የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ
2. አቶ ሰለሞን ሥዩም - የአንድነት የ"ሚሊዮኖች ድምጽ" የኢዲቶሪያል ቦርድ አባል
3. አቶ ስንታየሁ ቸኮል - የአዲስ አበባ የወጣቶች ክፍል ሃላፊ
4. አቶ ነዋይ ገበየሁ - የአንድነት የሕዝብ ግንኙነት ም/ሃላፊ እንደሚገኙበት ለመረዳት ተችሏል።

በነገው ዕለት በአዲስ አበባ፤ በባሕር ዳር፤ በአርባ ምንጭና በሌሎችም ቦታዎች ሊካሄድ የታሰበው የተቃውሞ ሰልፍ አገዛዙና የምርጫ ቦርድ ተበዬው የአንድነትና የመኢአድ ድርጅቶችን በግንቦት ወር ሊደረግ ከታሰበው ሀገራዊ ምርጫ ውጪ እንዲሆኑ ለማድረግ እየተሸረበ ያለውን ሤራ በመቃወም ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ የዓለምአቀፉ ማህበረሰቡ፣ በተለይም ለጋሽ ሀገሮች፣ ኢትዮጵያውያን ሕጋዊ መብቶቻቸው ለማስከበር በሰላማዊ መንገድ በሚያደርጉት ትግል ምክንያት አገዛዙ እየፈጸመባቸው ያለውንና ሊያባብሰው የሚችለውን አፈና፤ እስራትና የግፍ ተግባር በመገንዘብ ይህ ኢሰባአዊ ተግባር እንዳይፈጸም ተጽዕኖ በማድረግ ከአሁኑ እርምጃ እንዲወስዱ ለማሳሰብ ይወዳል።

ገዢው ፓርቲም በዜጎቹ ላይ ከሚፈጽመው የማሳደድ፤ የማሰርና ሌሎችም የግፍ ተግባሮች በአስቸኳይ እንዲታቀብ እናሳስባለን።

ሸንጎ መሠረታዊ መብቶቹን ለማስከበር ከሚታገለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ይቆማል። ለነዚህም መብቶች እውን መሆን ከሚታገሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ያለውን የትግል አጋርነት ያረጋግጣል።

በያንዳንዱ ፖለቲካ ድርጅት ላይ የሚካሄድ ሴራና ረገጣ በሁሉም ላይ የሚካሄድ ሴራ መሆኑን በመገንዘብ የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራ በመቆም በህዝብና በተቃዋሚዎች ላይ የተቃጣውን ጥቃት እንዲቋቋሙ ጥሪ እናደርጋለን።

መሠረታዊ መብቶችን ለማስከበር ትግሉ ይቀጥላል!

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : **shengo.derbiaber@gmail.com**